# ስለ አማራው ግልፅ እንሁን

## (ብአዴን፤ሕወሐትና ኦሕዴድ/ኦነግ አማራውን ለማጥፋት በራሱ አንጡራ መሬት ላይ የኦሮሞ ልዩ ዞን ብለው በፈጠሩት ግዛት ሰሞኑን አማራ የሆነ ሁሉ በታጠቁ የኦሮሞ አክራሪ ኀጠኞት ከባቲ፤ቀሚሴና ደዋ ጨፋ አማራ የሆነ ሁሉ እየተገደለ፤ እየተፈናቀለ፤ ወደ አፋር ክልልና ደቡብ ወሎ አገሩን ጥሎ በመሸሽ ላይ ይገኛል። በሌሎች ክልሎች የነበረው አደጋ ዛሬ አማራው ልክ እንደ 16 ኛው መቶ ክፍለዘመን በኦነግና ኦሕዴድ ካድሬዎችና ታጣቂዎች ደሙ እየፈሰሰና አገሩን እየተቀማ ነው። አማራ እርምጃ ላይ ያተኮረ ትግል ውስጥ መግባት ካልቻለ መጨረሻው የሚያምር አይሆንም። በጠራራ ፀሐይ ታሪክ ተደገመ! አማራው በቅም ቅም ዓያቶቹ ጉልት ተፈናቀለ። የብአዴን የስራ ውጤት ይህ የግፎች ግፍ ነው)

የአማራ ነገድ የታሪክ መሰረቱን ያለምንም ማዛባት ማየት በተሳናቸው ግለሰቦችና ባለፉት 50 ዓመት በፀረ አማራነት ዙሪያ ከተሰባሰቡት ሻቢያ፤ኦነግና ወያኔ ወዘተ. ዘርፈ ብዙ ጥፋቶችና ቅስቀሳ አማራው ዛሬ በኢትዮጵያ ቤተስኪያን እንደገባች ውሻ የሚደቆስና የተጠላ ሕዝብ ሆኖዋል። ለዚህም ማስረጃው ላለፉት 27 ዓመቶች የተፈፀመበት የዘር ማጽዳት ወንጀል መሬት ላይ የረገጠ ማስረጃ ስላለን ሌላ ምክንያት ማቅረብ አያሻም። አሁን በአገሪቱ ማዕከላዊ የፖለቲካ ስልጣን የሙጥኝ ብሎ ከያዘው ኢሕአዴግ ጀምሮ ኦጋዴንን፤አፋርን፤ደቡብን፤ጋምቤላን፤ቤኒሻንጉልን፤ትግራይንና ራሱ አማራ የተባለውን የሚገዙት ባደባባይ ጨፍጭፈውታል፤መጤ እያሉ አፈናቅለውታል፤ንብረት አልባ ተድርጎ በድህነት እንዲደቅ፤በመሰረተ ልማት ከጅራት ጫፍ እንዲኀተት፤በሕክምና እጦት እንዲሰቃይ፤ወልዶና ከብዶ ራሱን እንዳይተካ፤በት/ት ሁዋላቀርነት የተማረ አዲስ ትውልድ እንዳያፈራ፤ራሱን በራሱ ተከብሮ እንዳያስተዳድር፤አዘቅት ውስጥ እንዲኖር ብቻ ተዘርዝሮ በማያልቅ ጫና ማንነቱ በቅፍ ላይ ያለና መሪ እንዳጣ የንብ መንጋ ተበትኖ በሰቆቃ እንዲኖር(ኑሮ ካሉት. . .) ተፈርጆ የነገውን ዕጣ ፋንታው ምን ሊሆን እንደሚችል ሳይገባው በውዥንብር ውስጥ ገብቶ ይገኛል።

አማራው በአብዛኛው ባላገርና ገበሬ ነው። አብላጫው መደበኛ ት/ት የሌለው ስለሆነ ማንበብና መፃፍ አይችልም። ሰነድ ላይ ፊርማውን የሚያኖረው በአውራ ጣቱ ቀለም ነክሮ አሻራውን በማኖር ብቻ ነው። በዚህ ባለፉት አስተዳደሮች በመሀይምነት እንዲደቅ ሆን ተብሎ በደል ስለተሰራበት የቤተክርስትያን እንዲሁም የመስጊድ አገልጋዮች ከሚሰጡት ኀይማኖታዊ ሰበካ ውጪ አስተሳሰቡና አመለካከቱ ሊያልፍ አልቻለም። ይህ ሀቅ ግን አማራው በሚከተላቸው ኀይማኖቶች ፅኑና ፈሪሀ እግዚአብሔር እንዲኀናፀፍ ስላደረገው በባህሪው ቀናና ደግ እንዲሁም ሰላማዊ እንዲሆን አድርጎታል። ያለችውን አካፍሎና አብሮ በልቶና ጠጥቶ መኖርን የሙጥኝ ያለ ሚስኪን፤የዋህና አዛኝ ሕዝብ ነው። ነገር ግን የሚኖርባት፤የሞተላት አጥንቱን ከስክሶ የተመሰረተችው ኢትዮጵያን ማመን ከሚቻለው በላይ ስለሚወዳት በታሪክ በተከታታይ የደረሱበትን ጭፍጨፋዎችና የመሬት ዘረፋዎች ሳያጋንንና ተበዳይ ነኝ ሳይል የዮዲት ጉዲትን፤የአህመድ ግራኝን፤የኦሮሞ ወረራና መስፋፋት፤የአጼ ዮሀንስን ደቾሽ አገዛዝ፤የጣሊያንን ወረራና የዘር ብሎም ቅርስ ማጥፋት፤የደርግን ግፈኛ ሥርዓት ጥፋቶች ይቅር ብሎ የኖረ ሲሆን አሁን ላይ ደግሞ ኢሕአዴግ ለ 27 ዓመት ዘሩን እያጠፋው እያለ ለመጥፋት በመገዝገዝ ላይ እንደሆነ ጭራሹን ለመረዳት ተስኖት በማለቅ ላይ የሚገኝ አሳዛኝ ሕዝብ ሆኖዋል።

ኢሕአዴግ ስልጣን ከያዘ ከግንቦት 20/1983 እ.ኢ.አ ጀምሮ "አማራ ቀንደኛ ጠላታችን ነውና መጥፋት አለበት" ብለው በተነሱ ጠባብ ጎጠኛ የወያኔ ትግሬዎችና ከሁሉም ጎሳዎች ከተውጣጡ የዛሬ የኢትዮጵያ ፈላጭ ቆራጭ ገዥዎች ማንነቱን፤ግዛቱን፤ዜግነቱን፤ባጠቃላይ ስብዕናውን በጉልበት ተነጥቆ ሌት ተቀን እፍዳውን ያያል። እ.አ.አ በ 2007 በተደረገው ቆጠራ 2.5 ሚሊዮን አማራ የገባበት ጠፋ ብላ የኦህዴድ አመራርና በዛን ወቅት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ መስሪያ ቤት ኀላፊ በፓርላማ ውስጥ ባቀረበችው ሪፖርትና ማብራሪያ መናገርዋ አይረሳም። እቺ በፀረ አማራነት መርዝ ክፉኛ የተለከፈቺው ግፈኛ ለዘረኞቹ አማራውን በሀሰት አናሳ ለማድረግ ለሰራችው ወንጀል አምባሳደር ሆኖ የመሾም ስጦታ አግኝታበታለች። ዛሬ ደግሞ በጎጠኛው መንግስት ቁጥጥር ስር ያለው የምርጫ ቦርድ ሀላፊ ሆና በጠ/ሚ አብይ ተሾማለች። ለላ አዲስ የሕዝብ ቆጠራ በቅርቡ ሲደረግ የአማራው ብዛት ስንት ሊሆን እንደሚችል ካሁኑ መገመት የሚቻለን ቢሆንም ጉድና ጅራት ከበስተሁዋላው ነው እንደሚባለው በአማራው ላይ የሚሰራውን ሸፍጥ ግዜው ሲደርስ የምንሰማው ይሆናል። በዚህ አማራውን ለማዋደቅ በተደረገው ሴራ ብአዴን ተብሎ አማራው ላይ በተጫነው የወያኔ ትግሬዎች አሻንጉሊት መሪ አዲሱ ለገሰ በዛን ወቅት ም/ጠ/ሚር፤የግብርና ሚ/ርና የሕዝብ ቆጠራ ኮሚቴ ሰብሳቢ "ውጤቱን አስመልክቶ የቀረበው ሪፖርት ሙሉ በሙሉ ትክክል ነው" ሲል መደመጡንም እናስታውሳለን። ይህ እኩይ የሆነ ቅጥረኛ አማራ ሳይሆን የአማራ መሪ ሆኖ እስከ ቅርብ ግዜ ደግሞ የፌደራል ልዩ የድጋፍ ሰጪ ቦርድ ብሎም "የመለስ" አካዳሚ ሀላፊ ሆኖ ዘርፈ ብዙ ውድመቶችን በአማራው ላይ የፈፀመና ያስፈፀመ መሰሪ የአማራ ሕዝብ ጠላት ነው። በ 27 ዓመት ውስጥ አንዲት ቀን ስለአማራው ጭፍጨፋና መፈናቀል ትንፍሽ ብሎ አያውቅም። ብአዴን ደግሞ "እየተለውጥኩ ነው" የሚለውን ባዶ ቅስቀሳ ወደ ተዓማኒነት ማዞር ከፈለገ ይህን አጥፊ ፀር ከድርጅቱ አመራር ማስወገድ አለበት በሚል በአገር ውስጥም ሆነ ውጪ ያለንው አማራዎች የምንጎተጉተው ምክንያታዊ ሆነን ነው።

የአማራውን ብሔረተኛ ተጋድሎ ያቀጣጠለው የወልቃይት፤ ጠገዴና ጠለምት አማራ መሬት በግልበተኛው ሕወሐት በመዘረፉና አማራው ለግድያ፤እስርና ስደት ወዘተ. የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞበት አገሩ በመጤ የትግሬ ሰፋሪዎች ለዛውም የወያኔ ታጋዮች በነበሩ ጨካኝና አዕምሮዐቸው በአማራ ጥላቻ በተሞላ ታጣቂዎች በመወረሩምክንያት ነው። በነዚህ የጎንደር አማራ እርስቶች አማራ በራሱ ምድር ባይተዋር እንዲሆን ተድርግዋል። ለምሳሌ የአማራው ተጋድሎ በተጋጋለበት ወቅት ላይ የቀድሞው የትግራይና የወያኔ መሪ አውስትራሊያ በመሄድ በዚሁ ጉዳይ ትግራይ ከማንም ሀይል ጋር እንደማትደራደር ቅስቀሳ ሲያደርግ ብአዴንን ወክሎ አብሮት የተጉዋዘው የአማራ ብድርና ቁጠባ ተቕም(አብቁተ) ሀላፊ መኮንን ማንያዘዋል ለታላቅ ትግራይ ደጋፊዎች "ወልቃይት የትግራይ እንጂ የአማራ አይደለችም፤ ሕዝቡም ትግራዋይ ናቸው" ሲል የቅስቀሳው አካል በመሆን የተናገረውን ማን ይረሳለታል። ከሁሉም የሚገርነው ይህ በሆነ በጥቂት ግዜ የአማራ ክልልና የትግራይ ክልል መሪዎች ተፈራርመው አማራ ግጨውን ለትግራይ በማስረከብ በመካከላቸው ያለውን የድንበር አለመግባባት ለአንዴና መጨረሻ መቕጫ አበጁለት ተብሎ በዜና ሰማንው። በወልቃይት ጉዳይ የተነሳ በባህርዳር፤ በጎንደር፤በአንቃሽ፤ወዘተ. ስንቱ አማራ ወጣት በግፍ ተቀጠፎ ደሙ ደመ ከልብ ሆነ? ስንቱ ወላጅ ለቁም  ነገር ይደርሱልኛል ያላቸውን ልጆቹን በጨካኞቹ የወያኔና ብአዴን ታጣቂዎች ተሰለበ? ታዲያ እንዚህ ለትግሬ የበላይነት ያደሩ የብአዴን ባለስልጣኖች ሳይነቀሉ ተለውጫለው ማለት ይችላልን?

ጠ/ሚር አብይ ከመጡ ወዲህ የወልቃይት ጠገዴ አማራ ማንነት ኮሚቴ እንደገና ከስርና የግፍ

እንግልት በሁዋላ እንዲንቀሳቀሱ ሲደረግ እርሳቸውም ሆነ ብአዴን በኢሕአዴግ የውስጥ አሰራር ደንብ የትግራይ ጥቅም በማይነካበት መልኩ የወሰኑት እያለ ባደባባይ ጉዳዩ በሕገመንግስቱ መሰረት ወሳኔ ያገኛል የሚል የአዞ እንባ አሳይተውናል። ውጦ ማልቀስን አሁን ምን አመጣው? አብይ እኮ መቀሌ ላይ ስለጉዳዩ ነገሮችን አድበስብሰው ማርሽ በመለወጥ "ዳያስፖራዎች አርማጭሆና አብርሀጅራ መጥተው ልማቱን ባዩት. . . " ነበር ያሉት። የተጠቀሱትን መሬቶችንም የትግራይ ናቸው ለማለት ፈልገው ይሆን? ወይስ ወልቃይትና አርማጭሆን መለየት ተስኖአቸው?ጎንደር ላይ ደግሞ "በሕገመንግስቱ መሰረት. . . " የሚል ነገር አነሱ። አሁን ደግሞ የአማራ ማንነቱ ኮሚቴ ይፋ ባደረገው ዜና የፌደሬሽን ም/ቤት ሰብሳቢዋ የሕወሐት ማ/ኮ አባል ጥያቄያቸውን ውድቅ እንዳደረገችው ሰማን። እንግዲህ ብአዴን ምን ሊውጠው ነው? አማራው ከዳር እስከዳር ወልቃይት-ሁመራ፤ጠገዴና ጠለምት፤መተከል፤አላማጣና ራያ ወዘተ. የአማራ ናቸው ብሎ አንድ ዓይነት ታሪካዊ አቅም ይዞ ለመጀመሪያ ግዜ አደባባይ ወጥቶ ይገኛል። ታዲያ ተለወጥኩኝ የሚለው ብአዴን ድራማ በሚሰራበትና እገዛዋለው የሚለውን አማራ ይከተለዋል ወይ? ጉዱ ገና ነው ብዙ እናያለን።

አዲሱ ጠ/ሚር ከመጡ አንስቶ ብአዴን ወጣቱን በየቀበሌው እየሰበሰበ እባካችሁ ስሙኝ እኔ እኮ ታድሼያለሁ፤ በአዲስ መንፈስ ለልማታችሁ ዲሞክራሲያዊ ብሔረተኝነትን አንግቤ ወዘተ. በሚል ፊሽካ መንፋት እየነቃና በአማራ ብሔረተኝነት ዙሪያ ራሱን ለማዳን እየተደራጀ ያለውን አማራ ለማዘናጋትና ከገባበት አዘቅት እንዳይወጣ በኢትዮጵያዊነት የውሸት ቅስቀሳ እያጦዘው ይገኛል። ግን እውነታው ዛሬም አማራው መጤ ተብሎ ይገደላል፤ይፈናቀላል። አብይም ቢሆኑ ይህንኑ ባዶ ነገር በቃላቸው ሲያስተጋቡ "በኢትዮጵያ ውስጥ ድንበር የለም. . ." ይሉናል። ቢሆን ጥሩ ነበር ነገር ግን ራሳቸው በሚመሩትና በሚዘውሩት ኦሮሚያ ከሚባለው የአማራው መሳደድና መጨፍጨፍ መቼ ቆመ? በሌሎቹም ክልሎች እንደ ድሮው ቀጥሎና ብሶበት አይደለምን ያለው? እውነት ኦሕዴድና ብአዴን ኢሕአዴግን ለውጠናል ካሉ በአገሪቱ መፈናቀልን ወንጀል የሚያደርግና ሊያቆመው የሚችል ሕጋዊ ማዕቀብ በፓርላማቸው እንዲ ታወጅና ሕዝቡ እፎይ እንዲል የማያደርጉት ለምንድር ነው? ዞሮ ዞሮ የሚሉት እውን ከሆነ በሸንጎው የሁለቱ ድምጽ ብቻ አይበቃም ነበርን? አንባቢያን እስቲ ይህን በጥሞና አስቡት። አማራ ከእንግዲህ ወዲያ በተለይም ወጣቱ ይህን ከንቱ ውዳሴ የማይቀበልበት ደረጃ ላይ ደርሶዋል። በኢትዮጵያዊነትና በፈሪሀ እግዚአብሔርም የተሸበበው ሚስኪኑ የአማራ ገበሬም ልጆቹን እያየ መንቃቱና መነሳቱንስ እነ ብአዴን የመረዳት አቅም አላቸው? በኔ አመለካከት አንዴ ሕዝቡን ስለናቁት የት ይደርሳል በሚል ልክ ዶሮን ሲያታልሉዋት. . . እንደሚባለው ዛሬም ላይ መስመር መለወጥ የተሳናቸው ይመስለኛል። ይህ ደግሞ ባህርዳርና አዲስ አበባ ላይ ለተኮፈሱት ከፍተኛ አመራር ለሚባሉት አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ የሚለውን አገላለፅ ያሉበትን ሁኔታ እንዲረዱት እቸራቸዋለሁ።

ብአዴንና ከፍተኛ አመራሩን አስመልክቶ እ.አ.አ.በጁላይ 15/2014 'Amhara National Democratic Movement: A TPLF Surrogate and Watchdog Dominated by Tigryans Marching On Unchecked Destroying Amhara' በሚል ርዕስ ECADF ላይ ያወጣሁት ጽሁፌን በማንበብ የዚህን የወያኔ አውዳሚ ስብስብ ለአማራ የሚቆረቆር ሁሉም ሰው በራሱ በኩል ያለውንና እስካሁን የማናውቃቸውን ማስረጃዎች በተገኘው አጋጣሚ ተጠቅሞ ለሕዝብ በማጋለጥ በአገርም በውጪም አማራው ላይ እየደረሱ ያሉት የዘር ማጥፋት ወንጀሎች ያለ ገደብና ያለ ማቋዋረጥ እንዲታወቁ ጠንካራ ትግል ማድረግ አለብን። ይህን በምልበት ግዜ ዛሬ ላይ

በአማራው ስም የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎችና የሲቪክ ማህበራት እንዲሁም እንደ ወልቃይትና ኢትዮ ፓትሪዮትስ ወዘተ. ማህበራዊ ድህረ ገፆችን አስተዋፆ በማስፋፋትና አንድ ወጥ የሆነ የአማራ ሚዲያ ተቅም ምስረታን እውን ለማድረግ የሚደረገውን ርብርቦሽ ስመለከት ከአምስት ዓመት በፊት ስለአማራ በደሎች የሚሰሙ ድምጾች እጅግ በጣም ኢምንት እንደነበሩ በማስታወስ ጭምር ነው። ሌሎቹ 40 ና 50 ዓመት የፈጀባቸውን የአማራው ብሔረተኝነት በጣት በሚቆጠሩ ዓመቶች እዚህ መድረሱና በተለይም በአገር ቤት ወጣቱ የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ በመመስረቱ ቆሽቴ እየደበነ በቃ አማራዎች ተበትነናል ልንጠፋ ነው በሚል ሲደብን የኖረው ቆሽቴ አሁን ላይ ከጠባሳው እየሻረልኝ ይገኛል። ሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ ነውና አማራ ሆይ! ህልውናህን ለማዳን የጀመርከውን ብሔረተኛ ትግል ተደልለህ እንዳታቆም! ከምንግዜውም በበለጠ ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አለበለዚያ ድንጋይ ነው ብለው ይወረውሩሀል ስለሆነ አማራ ራሱን በመውደድ ከመታገል ውጪ አማራጭ የለውም። አብነት ሁነኛው ነኝ!